የቅድመ ዝግጅት ማስታወቂያ

የህግ ትምህርት መውጫ ፈተና ለመፈተን በዝግጅት ላይ ለምትገኙ ተፈታኞች

የህግ ትምህርት መውጫ ፈተና ቀደም ሲል በተገለፀው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ከግንቦት 29 እስከ ሰኔ 3 ቀን 2014 ዓ.ም ለመስጠት የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን በመሰራት ላይ እንገኛለን።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የተፈታኞች ምዝገባ አንዱ እና ዋንኛው የቅድመ ፈተና አሰጣጥ ዝግጅት ተግባር ሲሆን ተፈታኞች ከታች የተዘረዘሩትን ነጥቦች ትኩረት በመስጠት ግንዛቤ እንዲጨብጡ እናሳስባለን።

1. የምዝገባ ቀናት ማስታወቂያ - የተፈታኞች የምዝገባ ቀናት ከጥቂት ቀናት በኋላ ሲወሰን ለሁሉም አስፈታኝ ዩኒቨርሲቲዎች በደብዳቤ እና ለተፈታኞች " አለ " በሚለው የቴሌግራም ቻናል ይፋ ይደረጋል።

2. የምዝገባ ቀናት ጊዜ ሰሌዳ ቆይታ - ከተፈታኞች ምዝገባ መጠናቀቅ በኋላ የፈተና ህትመት የሚካሄድበት ወቅት በመሆኑ እና ፈተናውን በጊዜ ሰሌዳው መሰረት ለመስጠት ያለው ጊዜ አነስተኛ በመሆኑ የተፈታኞች ምዝገባ ቀናት ቆይታ የተፈታኞች ምዝገባ መጀመሩ በደብዳቤ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ ሰባት የስራ ቀናት ብቻ ይሆናል።

3. ተፈታኞች ለምዝገባ እና ለመፈተን ሲመጡ በተጨማሪ ግንዛቤ የሚያስፈልጋቸው ሁኔታዎች -
   - 3.1 በሚማርበት ዩኒቨርሲቲ ፈተናውን ለመውሰድ የተፈቀደለት እና የተመዘገበ መሆን አለበት፣
   - 3.2 ለምዝገባ የተወሰነውን ክፍያ በዩኒቨርሲቲው ባንክ ሂሳብ ቁጥር ብቻ ገቢ ያደረገ መሆን አለበት፣ ከዩኒቨርሲቲው ባንክ ሂሳብ ቁጥር ውጭ በሌላ ተቋም ገቢ በማድረግ ደረሰኝ ማቅረብ ወይም ከምዝገባ ጊዜ ሰሌዳ ውጪ ለዩኒቨርሲቲውም ገቢ በማድረግ ደረሰኝ ማቅረብ ተቀባይነት የለውም፣ ፈተና ላይ ለመቀመጥም አያስችልም፣
   - 3.3 ለመፈተን የተመዘገበ ስለመሆኑ በዩኒቨርሲቲው በኩል ስሙ ለኢንስቲትዩቱ የተላከ መሆን አለበት፣ በምዝገባ ጊዜ ገደብ ውስጥ ብቻ ስሙ በዩኒቨርሲቲው መዝጋቢነት እና በኢንስቲትዩ ማረጋገጫ ያልተላለፈ ተመዝጋቢ ፈተና ላይ መቀመጥ አይችልም፣
   - 3.4 ወደፊት በሚገለፀው የምዝገባ ጊዜ ሰሌዳ ብቻ የሚፈተንበትን ዩኒቨርሲቲ ምርጫ እንዲሁም በኤግዘምሽን ምክንያት የማይፈተናቸው ፈተናዎች ካሉ ማሳወቅ አለበት፣ ከምዘገባ ጊዜ ሰሌዳው ውጭ የሚቀርብ ኤግዘምሽን መረጃ እና የዩኒቨርሲቲ ለውጥ ተቀባይነት የለውም፣
   - 3.5 በምዝገባ ወቅት የሚፈተንበትን ዩኒቨርሲቲ ምርጫ ሲመርጥ ከተማረበት ዩኒቨርሲቲ ርቆ የሚገኝ ከሆነ ህጋዊ ምክንያት (የመስሪያ ቤት መታወቂያ፣ የነዋሪነት መታወቂያ፣ አስገዳጅ የስራ ወይም የፀጥታ ሁኔታ መረጃ፣ የሆስፒታል መረጃ፣ ሌሎች) ማሳየት / ማቅረብ አለበት፣ ጉዳዩም ለኢንስቲትዩቱ በደብዳቤ መድረስ ይገባዋል፣ በፈተና አሰጣጥ ወቅት የተፈታኞች መረጃ ማጣራት ሲደረግ ስህተት ሆኖ ከተገኘ ፈተናው ይሰረዝበታል፣
   - 3.6 ከተማረበት ዩኒቨርሲቲ ውጭ ተመዝግቦ የተገኘ ተፈታኝ ወይም ያላስተማረውን ተማሪ መዝግቦ መረጃ ያስተላለፈ ዩኒቨርሲቲ የምዝገባው መረጃ ውድቅ የሚደረግበት ሲሆን ኃላፊነቱን ተፈታኙ / ዩኒቨርሲቲው የሚወስድ ይሆናል፣ ፈተና ላይ ለመቀመጥም አያስችልም፣
   - 3.7 በጊዜ ሰሌዳው መሰረት ዩኒቨርሲቲዎች የተመዝጋቢዎች ዝርዝር እና የተሰበሰበ ገንዘብ ገቢ ካላደረጉ ምንም ተፈታኝ እንዳልመዘገቡ ይቆጠራል / ኃላፊነት ይወስዳሉ፣
   - 3.8 በፈተና አሰጣጥ ወቅት ማንነትን የሚገልጽ ህጋዊ መታወቂያ፣ እስክሪቢቶ እና የተፈቀዱ ማጣቀሻዎችን ብቻ ይዞ መገኘት ይገባል፣
   - 3.9 በፈተና አሰጣጥ ወቅት ከተፈቀዱ ማጣቀሻዎች ውጪ ማንኛውንም ዓይነት ፅሑፍ ያለበት ወረቀትም ሆነ ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ፣ የእጅ ሰዓት፣ ተፈታኙ ከስራ መደቡ አንፃር ህጋዊ የሆነ ሆኖም በፈተና ጣቢያ የማይፈቀድ ነገር ይዞ መገኘት እንዲሁም ሌሎች በፈተና አሰጣጥ ወቅት የማይፈቀዱ ነገሮችን ይዞ መገኘት አይቻልም፣ በአራተኛው የፈተና ቀናት ማንነትን ከሚገልጽ ህጋዊ መታወቂያ እና ከእስክሪቢቶ በስተቀር ምንም ነገር ይዞ መምጣት አይፈቀድም። በቅድመ ፈተና ፍተሻ ወቅት በፈተና መስጫ ግቢ እና ክፍል ውስጥ ይህ ሆኖ ከተገኘ ሙሉ የፈተና ውጤት ይሰረዛል፣
   - 3.10 በፈተና አሰጣጥ ወቅት ምንም ዓይነት ነገር መቀያየር እና መዋዋስ የማይቻል በመሆኑ ሁሉም ተፈታኝ በግሉ የሚጠቀምበትን ነገር ይዞ መገኘት ይገባዋል፣
   - 3.11 የፈተና አሰጣጥ ከተጀመረ በኋላ በተለያየ ህጋዊም ሆነ ህጋዊ ባለሆነ ምክንያት ከሰላሳ ደቂቃ በኋላ አርፍዶ የሚመጣ ተፈታኝ ወደ ፈተና ግቢም ሆነ ክፍል ውስጥ መግባት አይፈቀድም፣ በመሆኑም ለፍተሻ ሂደት እና ለቅድመ ዝግጅት ሲባል ማንኛውም ተፈታኝ ፈተና ከሚሰጥበት ሰዓት አንድ ሰዓት ቀደም ብሎ ወደ ፈተና ጣቢያ ጊቢ እንዲደርስ ይመከራል፣
   - 3.12 ውጤትን በተመለከተ ቅሬታ ካለ በዩኒቨርሲቲ በኩል በደብዳቤ ለኢንስቲትዩቱ የሚቀርብ ይሆናል።

ኢንስቲትዩቱ - መልካም የቅድመ ዝግጅት ጊዜ!

ማስታወሻ - በቀጣይ ባሉት ቀናት እና ሳምንት ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ማስታወቂያዎችን ይከታተሉ / ለሌሎች ያሳውቁ።